**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

| | | |
|---|---|---|
| 3ki Diro Kiiro 25<br><br>Hawaasa, Woxawaajje 20, 2014 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho<br><br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፫ኛ ዓመት ቁጥር ፳፭<br><br>ሀዋሳ፣ ነሐሴ ፳ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም |


**Amado**

**Lallawu Kiiro 25/2014**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Hedeweelcho Dano, Wirro Gatamaratenna Agarooshshu Fande Uurrisate Fulino Lallawa ………. Qoola ….**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፳፭/፳፻፲፬**

**በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የድንገተኛ አደጋ፣ መልሶ ማቋቋሚያና መጠባበቂያ ፈንድ ለማቋቋሚ የወጣ አዋጅ……………. ገጽ ….**


## Lallawu Kiiro 25/2014

## Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Hedeweelcho Dano, Wirro Gatamaratenna Agarooshshu Fande Uurrisate Fulino Lallawa

Qoqqowu giddo diilallote gade soorramate korkaatinni kalaqantanno hedeweelcho dano mannu lubbonna dagoomu heeshsho aana gawajjo iillishanni noohura hedeweelcho dano iillishshanno gawajjo harancho yannanninna wiinamunni iillatenni manchu lubbonna jajja gatisa hasiissannohura,

Hedeweelcho dano kalaqanturo hasiissanno kaa'lo addi addi bissawiinni iillitanno geeshsha baycho wiinamunni iillatenni kalaqantara dandiitanno

## አዋጅ ቁጥር ፳፭/፳፻፲፬

## በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የድንገተኛ አደጋ፣ መልሶ ማቋቋሚያና መጠባበቂያ ፈንድ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በክልሉ ውስጥ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚከሰት ድንገተኛ አደጋ በሰው ህይወትና በማኅበረሰቡ ኑሮ ላይ ጉዳት እያደረሰ በመሆኑ የድንገተኛ አደጋ የሚያስከትለዉን ጉዳት በአጭር ጊዜ እና በፍጥነት በመድረስ የሰው ህይወትንና ንብረትን መታደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ድንገተኛ አደጋ ሲከሰት የሚያስፈልገውን እርዳታ ከተለያዩ አካላት እስከሚደርስ በስፍራው በፍጥነት በመድረስ ሊፈጠር የሚችለውን ጉዳት ማስቀረት

gawajjo hoola woy ajisha hasiissanota ammannoonnihura;

Danotenni gawajjantinnore kaa'latenna wirro gatamarate batinye bissa beeqooshshi noota agarooshshu fande uurrisa, gashshootu amuraatiseno gutamaanote beeqooshshe buuxisinoha, xawadimmanna xa'mamooshshe sirsannoha ikkanno gede seerunni gumula hasiissannota ikkite leelitinohura,

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Bayriidi Seeri quwa 48 cinaancho quwa 3(a) garinni aantete nooha lallamboonni.

**GAFA MITE**

**<u>XAPHOOMA WORO</u>**

1. **Harancho Umo**

   Konne lallawa "Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Hedeweelcho Dano, Wirro Gatamaratenna Balaxi-qixxaawote Fande Urrisate fulino Lallawa Kiiro 25/2014" yine woshshinara dandiinanni.

2. **Tiro**

   Qaalu horosi garinni wole tiro aannoha ikka hoogiro konni lallawi giddo:

   1. **"Qoqqowu"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti;
   2. "**Mootimma**" yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi mootimmaati;
   3. "**Komishiine**" yaa Sidaamu Dagoomu

ወይም ማሳነስ አስፈላጊ እንደሆነ በመታመኑ፤

የአደጋ ተጎጂዎችን ለመርዳት እና መልሶ ለማቋቋም የበርካታ አካላት ተሳትፎ ያለበት የመጠባበቂያ ፈንድ ማቋቋም፣ የአስተዳደር ሥርዓቱም የባለድርሻዎችን ተሳትፎ የሚያረጋግጥ፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን እንዲሆን በሕግ ማዕቀፍ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፫(ሀ) መሰረት የሚከተለዉ ታዉጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የድንገተኛ አደጋ፣ መልሶ ማቋቋሚያና መጠባበቂያ ፈንድ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፳፭/፳፻፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ክልል" ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፤
   2. "**መንግሥት**" ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፤
   3. "**ኮሚሽን**" ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ነው፤

Qoqqowi Mootimma Danote Yaaddo Loosu Massagooshshi Komishiineeti;

4. "**Fande**" yaa Jiro woxunninna Uduunnunni afi'nanni buichooti;
5. "**Danote Agarooshshu Fande**" yaa dano kalaqantanno yannara dano iillitinonsa bissa kaa'late hattono wirro gatamarate dandiisiisanno woxunninna udiinnunni addi addi buichonni gamba assinooni jirooti
6. "**Dano**" yaa kalaqamunni woy mannu assooti korkaatinni mannu heeshshonna jajju aana kalaqamanno qarrinni dano iillitinosi manni wolu bisi kaa'lo afi'ra hoogiro albi heeshshosi widira higa dandaannokkiri kalaqamiro yaa ikkitanna danono: moolletenni sununni iillitannota hattono lolahu, giirate, gaancete, kakkadishu, baattote huxi'ra, tigete toanna labbinore hedeweelcho dano amadanno;
7. "**Daase**" yaa danote korkaatinni mininsa diigameenna yannate geeshsha daase mi'nite heedhanno gede uynanninsa pilaastike, sharanna labbanno uduuneeti;
8. **"Kaa'lo"** yaa danote reqecci yitino manna woy jajja baote gatisate hasiissanore gallanniwa, sagale, wayinna labbinore gawajjamaano afidhanno gede uynannireeti;
9. **"Uurrinshu Kaa'lo"** yaa diru dirunkunni kalaqamunninna mannunni kalaqantanno danora kaa'lo afidhanno gede gumullannisa mannira mootimma uytanno kaa'looti;
10. "**Wirro gatamara**" yaa danote gawajjonni jajjinsa baeenna qaensanni darantino woy jawa gawajjo iillitinonsare dandaami bikkinni albi heeshshonsawa higganno gede kaa'late;

4. **"ፈንድ"** ማለት ሀብት በገንዘብና በዓይነት የሚገኝበት ምንጭ ነው፤
5. **"የአደጋ መጠባበቂያ ፈንድ"** ማለት አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ አደጋ የደረሰበት ወገን ለመርዳት እንዲሁም መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል በገንዘብ እና በዓይነት ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰበ ሀብት ነው፤
6. **"አደጋ"** ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያቶች በሰው ህይወት እና በንብረት ላይ በሚፈጠሩ ችግሮች አደጋው የደረሰበት ማኅበረሰብ የደረሰበት ጉዳት የሌላ አካል እርዳታ ካላገኘ በቀር የቀድሞ ኑሮውን መቀጠል የማያስችል ሁኔታ ሲፈጠር ማለት ሲሆን አደጋዎቹም፡- በድርቅ የሚደርስ አዝጋሚ አደጋ እንዲሁም የጎርፍ፣ የእሳት፣ የግጭት፣ የወረርሽ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መንሸራተት እና የመሳሰሉትን ድንገተኛ አደጋዎችን ያጠቃልላል፤
7. **"መጠለያ"** ማለት በአደጋ ቤታቸው ለፈረሰባቸው ሰዎች ጊዜያዊ መጠለያ እንዲሰሩበት የሚሰጣቸው እንደ ፕላስቲክ ሽት፣ ሸራ እና የመሳሰሉት ቁሳቁሶች ናቸዉ፤
8. **"ዕርዳታ"** ማለት ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን ወይም ንብረትን ለመታደግ የሚያስፈልጉ እንደ መጠለያ፣ ምግብ፣ ውሀ እና የመሳሰሉት ተጎጂዎች እንዲያገኙ የሚሰጣቸው ነው፤
9. **"መደበኛ ዕርዳታ"** ማለት በየዓመቱ በተፈጥሮና በሰዉ ሰራሽ በሚከሰተው አደጋ ዕርዳታ እንዲያገኙ ለሚወሰንላቸው ሰዎች በመንግሥት የሚሰጥ ዕርዳታ ነው፤
10. **"መልሶ ማቋቋም"** ማለት በአደጋ ጉዳት

11. “**Amaalete Mine**” yaa konni lallawi quwa 9 garinni uurrino hedeweelcho dano agarooshshu fande gashshanno amaale mineeti;
12. Konni lallawi giddo mitte koo-teemmanni worroonnihu horosi garinni wole koo-teemmano amadannoho.

## GAFA LAME

## AGAROOSHSHU FANDE UURRISA, EOTE BUICHONNA GASHSHOOTE

### 3. Fande Uurrisa

1. Hedeweelcho danonna wirro gatamarate agarooshshi fande (konni gedensaanni “fande” yine woshshinanniti) uurrinshu faynaansete buicho ikkite baxxitino baankete akkawunte giddo ofoltanno gede konni lallawinni uurrinsoonni.
2. Amaalete mini fandete loosira hasiissanno tantano komishiinete hundaanni deerru deerrunkunni uurrissanno.
3. Fande qoqqowu faynaanse biiro gashshitanno xaphi yitino fande gobbaanni ikkitanno.
4. Fandete anni Qoqqowu Mootimma ikkitanno.

### 4. Fandete Hexxo

Qoqqowu giddo afantanno jiro buusansiisatenni qoqqowu giddo babbaxxino korkaatinni kalaqantanno danora wiinamu kaa’lo aatenni mannu heeshshonna jajju aana iillitara dandiitanno gawajjo ajishate woy gawajjo

ንብረታቸው ወድሞባቸው ከቄያቸው የተፈናቀሉ ወይም ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ተጎጂዎች በተቻለ መጠን ወደ ቀድሞ ኑሮአቸው እንዲመለሱ መርዳት ነው፤

11. **“ምክር ቤት”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሰረት የተቋቋመው የድንገተኛ አደጋ መጠባበቂያ ፈንድ አስተዳደር ምክር ቤት ነው፤
12. በዚህ አዋጅ ውስጥ በአንድ ጾታ የተገለጸው ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመጠባበቂያ ፈንድ መቋቋም፣ የገቢ ምንጭ እና አስተዳደር

### 3. ስለፈንዱ መቋቋም

1. የድንገተኛ አደጋና መልሶ ማቋቋሚያ የመጠባበቂያ ፈንድ (ከዚህ በኋላ “ፈንድ” እየተባለ የሚጠራ) ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ በልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ተቀማጭ እንዲሆን በዚህ አዋጅ ተቋቁሚል፡፡
2. ምክር ቤቱ ለፈንዱ ስራ የሚያስፈልገውን መዋቅር በኮሚሽኑ ውስጥ በየደረጃው ያቋቁማል፡፡
3. ፈንዱ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ከሚያስተዳድረው የተጠቃለለ ፈንድ ውጪ ይሆናል፡፡
4. የፈንዱ ባለቤት የክልሉ መንግሥት ይሆናል፡፡

### 4. የፈንዱ ዓላማ

በክልሉ የሚገኘውን ሀብት በማስተባበር በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ምክንያት

iilliteennansa qaensanni darantino manni heeshsho wirro gatamarate dandiisiisanno woxunna jajju dhuka dhaawate.

**5. Fandete Eote Buicho**

Fande aantete noo bu'anni fushshinannita ikkitanno:

1. Diru dirunkunni mootimmatenni gaammanni irkote baajeette,
2. Gobbate giddoydi kaa'lo uytannorinna hojji dureeyye assitanno kaa'lo,
3. Qoqqowu dagawiinni gamba assinanni kaa'lo,
4. Wole addi addi eote buichonni ikkanno.

**6. Fandete Gashshoote**

1. Gamaba assinanni woxi komishiinete fandete su'minni fannanni baxxitino baankete akkawuntera eo ikkanno.
2. Udiinnichunni gamba assinanni jajja komishiinete addi magaziine giddo duunnanniha ikkanno.
3. Fandete gashshooti faynaansete amuraatenna seera agadhino garinni jeefamannoha ikkanna loosu aana hosannohu borde sayissanno muro garinni ikkanno.

**7. Fandete Horoonsishshu Safaraano**

Fandete gaammoonni baajete loosu aana hossannohu wooronni dirroonniri giddo mittu wo'mirooti:

1. Dano kalaqanturonna hajote Qoqqowu Amaale Mininni gaammonniti baajeette ikkado ikkitinokkita buunxiha ikkiro,
2. Hedeweelcho dano kalaqanturonna hajo

ለሚፈጠረው አደጋ አስቸኳይ እርዳታ በመስጠት በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ወይም ጉዳት ደርሶባቸው ከቄያቸው የተፈናቀሉ ሰዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል የገንዘብና የንብረት አቅም መገንባት ነው፡፡

**5. የፈንዱ የገቢ ምንጭ**

ፈንዱ ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

1. በየዓመቱ በመንግሥት የሚመደብ የድጋፍ በጀት፣
2. ከሀገር ውስጥ ለጋሾች እና ከግል ባለሀብቶች የሚገኝ እርዳታና ስጦታ፣
3. ከክልሉ ኅብረተሰብ የሚገኝ እርዳታ፣
4. ከሌላ ምንጭ የሚገኝ ገቢ ይሆናል፡፡

**6. ስለፈንዱ አስተዳደር**

1. የሚሰበሰበው ገንዘብ በኮሚሽኑ በፈንድ ስም በሚከፈተው ልዩ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ይሆናል፡፡
2. በዓይነት የሚሰበሰበው ንብረት በኮሚሽኑ ልዩ መጋዘን ውስጥ የሚከማች ይሆናል፡፡
3. የፈንዱ አስተዳደሩ የፋይናንስ ስርዓት እና ሕግ ተከትሎ የሚፈፀም ሲሆን ሥራ ላይ የሚውለውም በምክር ቤቱ ውሳኔ መሠረት ይሆናል፡፡

**7. የፈንዱ አጠቃቀም መመዘኛዎች**

ለፈንዱ የተመደበው በጀት ሥራ ላይ የሚውለው ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲሟላ ነው፡-

1. አደጋ ሲከሰት እና ለጉዳዩ በክልሉ ምክር ቤት የተመደበው በጀት በቂ አለመሆኑ ሲረጋገጥ፣

qorqorate illacha tuga hasiissanno yine muro sayinsiro,

3. Hedeweelcho dano looso massagate irko ikkitannonna baxxitino pirojekite jeefisiisate hasiissannota ammannoonniha ikkiro,
4. Fande garunni horoonsi'rate injiino gari hee'rasi buunxiro.

**8. Fandetenni Uynanni Kaa'lo**

Fandete gaammoonni baajeette woroonni dirroonni looso jeefisiisate hossanno:

1. Sagalenna sagale ikkinokki udiinni kaa'lora,
2. Qarqarunna way coichimma agarooshshe jeefisiisate,
3. Daase minate,
4. Hee'rate hasiisanno jajji irkonna woloota kalaqantino danora dawadhote hossanno damatte udiinnira;
5. Jajjinsa baino manna wirro gatamaratenna albi heeshshonsa widira higganno gara injeessate,
6. Fayyimmate danoranna xagga shiqishate,
7. Saadate sagalenna xagga hidhate;
8. Anganni waa shiqishatenna wole lubbo gatisate loosi aana hosanno.

## GAFA SASE

## HEDEWEELCHO DANO AGAROOSHSHI FANDE GASHSHOOTI AMAALE MINE

**9. Amaalete Mine Uurrisa**

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma hedeweelcho dano agarooshshi fande gashshooti Amaale mini konni lallawinni uurrino.

**10. Amaalete Mini Miilla**

Amaalete Mini aantete noo miilla heedhannose:

1. Qoqqowu Pirezidaantichi …….

2. ድንገተኛ አደጋ ሲከሰት እና ጉዳዩን ለመቆጣጠር ትኩረት መስጠት እንዳለበት ሲወሰን፣
3. ለድንገተኛ አደጋ አመራር ድጋፍ የሚሆኑና ልዩ ፕሮጀክቶች ማስፈፀም ተገቢ መሆኑ ሲታመን፣
4. ፈንዱን በአግባቡ ለመጠቀም ምቹ ሁኔታ መኖሩን ሲረጋገጥ ነዉ፡፡

**8. በፈንዱ የሚሰጥ እርዳታ**

ለፈንዱ የተመደበው በጀት ለሚከተሉት ሥራዎች ማስፈፀሚያ ይውላል፡-

1. የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ እርዳታ፣
2. ለአካባቢና ለውሃ ንፅህና አጠባበቅ ማስፈፀሚያ፣
3. ለመጠለያ፣
4. የመተዳደሪያ ጥሪት ድጋፍ እና ሌሎች ለተፈጠረው አደጋ ምላሽ የሚውሉ መሰረታዊ ቁሳቁሶች፣
5. ንብረታቸው የወደመባቸውን ሰዎች መልሶ በማቋቋም ወደ ቀድሞ ኑሮአቸው እንዲመለሱ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣
6. ለጤና አደጋዎችና ለመድኃኒት አቅርቦት፣
7. ለእንስሳት መኖ እና መድሃኒት ግዢ፣
8. የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሌሎች የማዳን ስራዎች ላይ ይውላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለድንገተኛ አደጋ መጠባበቂያ ፈንድ አስተዳደር ምክር ቤት

**9. ስለምክር ቤት መቋቋም**

የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የድንገተኛ አደጋ መጠባበቂያ ፈንድ አስተዳደር ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**10. ስለምክር ቤቱ አባላት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ……. ሰብሳቢ

Gambasaancho

2. Qoqqowu Laynki pirezidaantichi ……. Laynki Gambasaancho
3. Danote yaaddo Loosu Massagooshshi Komishiinere ……. Borreessaancho
4. Jeefisiisaanote amaale mini miilla ikkitino loosu minna sooreeyye ....... Miila
5. Qoqqowu Amma’note uurrinshubba 3 lekkisaano …… Miila
6. Gobbate geerinni 3 lekkisaano ..... Miila
7. Meentunna wedellu tantanonni 4 lekkisaano ..... Miila
8. Qoqqowu giddo loossanno sivile dagoomi uurrinshubbanni 3 lekkisaano ….. Miila
9. Hasishshu garinni qoqqowu pirezidaantichinni ledantanno uurrinshubbanna halanyu ……. Miila Ikkitanno.

**11. Amaalete Mini Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Amaalete mini aantete noo biilloonyinna loosu qeechi hee’rannose:

1. Dano balaxxotenni gargadhate kaa’litannonna dagoomu beeqqooshshe hasidhanno addi millimote loossa aliidimmatenni massaganno;
2. Addi addi danonni gawajjo iillitinonsa dagoomu bissanna qoxxeesubba wirro gatamarate loossa aliidimmatenni massaganno;
3. Fandete bikkanna dana lossate kaa’litanno addi addi bissa beeqooshshenna waaxo hasidhanno addi addi hayyo loosu iima hossanno gede gumulanno;

2. የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ..... ምክትል ሰብሳቢ
3. የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር ……. ፀሐፊ
4. የመስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆኑ የሁሉም መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች …….. አባል
5. ከክልሉ የሃይማኖት ተቋማት 3 ተወካዮች …….. አባል
6. ከሀገር ሽማግሌዎች 3 ተወካዮች ..... አባል
7. ከሴቶችና ወጣቶች አደረጃጀት 4 ተወካዮች ........ አባል
8. በክልሉ የሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች 3 ተወካዮች …….. አባል
9. እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚጨመሩ ተቋማት እና ግለሰቦች ...... አባል ይሆናሉ፡፡

**11. የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. አደጋዎችን አስቀድሞ ለመከላከል የሚረዱና የሕብረተሰብ ተሳትፎ የሚፈልጉ ልዩ የንቅናቄ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤
2. በተለያዩ አደጋዎች ጉዳት የደረሰባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎችንና አካባቢዎችን መልሶ የማቋቋምና ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣
3. የፈንዱን መጠንና ዓይነት ለማሳደግ የሚረዱና የተለያዩ አካላት ተሳትፎና ቅንጅት የሚፈልጉ ልዩ ልዩ ስልቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ይወስናል፤

4. Komishiine saadate, xeenu, gidu, sagalete waastinni gara lainohunni shiqqanno taje kaima assatenni uurrinshu keeno assitanno;
5. Komishiine shiqishshanno amaalete hedo garinni danote yaaddoranna tumora hasiissanno kaa'lo agarooshshu fande aaninnni assinanni gede muro sayissanno;
6. Qoqqowu danote bikkinna hekko xiinxallo guma keentanno; hattono dano kalaqamase faajje assitanno;
7. Kalaqantara dandiitanno dano gargarate dandiisiissanno irkote mixo kaajjishshanno;
8. Komishiine amaalete mini gumulo ha'runsatenni fandete baajeette loosu aana hosiissanno;
9. Komishiinetenni qixxaabbanno kaa'lo gamba assate sanadda kaajjishshanno;
10. Yannannita qoqqowu rippoorte kaajjishshanno;
11. Agarooshshu fande jiro hasi'noonni hexxora hosase ha'runsitanno; buuxxanno.

12. **Amaalete mini Gambasaanchi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Gambasaanchu:

1. Amaalete mini gambooshshe woshshanno; massaganno;
2. Amaalete mini gumulo loosu aana hosase buuxanno;
3. Amaalete mine lekkise sayki wogane ledo xaadooshshe assanno;
4. Amaalete mini aanno ledote loossa jeefisanno.

4. በኮሚሽኑ አማካይነት ስለእንሳስት፤ ዝናብ፣ ሰብልና የምግብ ዋስትና ሁኔታ አስመልክቶ በሚቀርብ መረጃ በመመርኮዝ ቋሚ ግምገማ ያደርጋል፤
5. ኮሚሽኑ በሚያቀርበው ምክረ-ሀሳብ መሰረት ለአደጋ ስጋትና ምላሽ የሚያስፈልገው ከመጠባበቂያ ፈንድ ላይ እርዳታ እንዲደረግላቸው ይወስናል፤
6. በክልሉ የአደጋ ስፋትና ተፅዕኖ ጥናት ውጤት ይገመግማል፤ እንዲሁም አደጋ መከሰቱን ይፋ ያደርጋል፤
7. ሊከሰት የሚችለውን አደጋ ለመከላከል የሚያስችል የድጋፍ ዕቅድ ያፀድቃል፤
8. ኮሚሽኑ የምክር ቤቱን ውሳኔ በመከተል የፈንዱን በጀት ያንቀሳቅሳል፤
9. በኮሚሽኑ በሚዘጋጀው ስለእርዳታ አሰባሰብ የሚመለከት ሰነዶችን ያፀድቃል፤
10. ወቅታዊ የክልሉን ሪፖርት ያፀድቃል፤
11. የመጠባበቂያ ፈንዱን ሀብት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፡፡

12. **የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር**

ሰብሳቢው፡-

1. የምክር ቤቱን ስብሰባ ይጠራል፤ ይመራል፣
2. የምክር ቤቱ ውሣኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣
3. ምክር ቤቱን በመወከል ከሦስተኛ ወገን ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤
4. ከምክር ቤት የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

13. **Amaalete Mini Borreessaanchi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Borreessaanchu:

1. Amaalete mini gambooshshi ajanda qixxeessatenni amaalete mini gambasaanchira shiqishanno;
2. Amaalete mini gambooshshi songaale amadanno;
3. Ayee amaalete mini tajubba, mareekkuwanna sanadda amadate yawo noosi;
4. Amaalete mini aanno woloota loossa jeefisanno.

14. **Amaalete Mini Gambooshshi Amuraate**

1. Amaalete mini sasu aganinni mitte higge gambooshshe assanno. Ikkollana wiinamu ikkito xaadduronna gambasaanchu woshshiro ayee yannara gambooshshe assara dandaanno.
2. Amaalete mini miilla mereerinni bocu aleenni ikkitannori leelturo gambooshshu guutaho.
3. Amaalete mini gumulo huurote roorrenni sayissanno. Ikkollana huuro lamenkawa taalte beehanturo gambasaanchu huuro uyno gaamoti amaalete mini gumulo ikkitanno. Ayee gumulote badooshshi borreessamanno.
4. Konni quwira xawinsoonniri noo gedeenni hee'reenna amaalete mini umise gambooshshu amuraati biddissa fushshara dandaanno.

**GAFA SHOOLE**

13. **የምክር ቤቱ ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር**

ፀሐፊው፡-

1. የምክር ቤቱን የስብሰባ አጀንዳዎች በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ ያቀርባል፤
2. የምክር ቤቱን የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤
3. ማናቸውም የምክር ቤቱን መረጃዎች፣ መዛግብትንና ሠነዶችን በኃላፊነት ይይዛል፤
4. ከምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

14. **የምክር ቤቱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት**

1. ምክር ቤቱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ ሆኖም አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥምና ሰብሳቢው ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. ምክር ቤቱ ውሣኔውን በአብላጫ ድምጽ ያስተላልፋል፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል ከተከፈለ የሰብሳቢው ድምጽ ያለበት ወገን የምክር ቤቱ ውሣኔ ይሆናል፡፡ ማንኛውም የውሣኔ ልዩነት ይመዘገባል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ የተገለጹት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**ክፍል አራት**

## ADDI ADDI WORO

15. **Loosu Aana Hosikkinni Gatino Kaa'lote Woxenna Jajja**

Kuni lallawi fulara albaanni kaa'lotenna wirro gatamarate loosira hende gamba assineenna loosu aana hosikkinni gatino woxinna jajji konni lallawinni fandete widira soorraminno.

16. **Elaanote Qoosso**

Fandete irko assitannno bissa woxunni ikko udiinnunni uytino jiro hasi'noonni hexxora hosase xa'mate qoosso heedhannonsa.

17. **Shallagote Taje**

1. Fande wo'manna halaalaancho shallaggote taje amaddanno.
2. Fandenniti shallagote tajubbanna woxu sanadda Qoqqowu Qara Odiitere loosu mininni woy qara odiitere riqiwanno wolootu odiiterootinni diru dirunni qorqoranni.
3. Odiiterootunnihu buuxote gumi diru dirunku goofimarchira amaalete minira shiqanno.

18. **Jeefishshu Nookki Seerinna Asooti**

Konni lallawi ledo kiphi yaanno ayee seeri woy rosamino assooti konni lallawinni hanqafantino hajora jeefishshu dihee'rannosi.

19. **Wodhonna Biddissa Fushshate Biilloonye**

1. Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Mini konne lallawa loosu aana hosiisate wodho fushshara dandaanno.
2. Amaalete mini konne lallawanna konne quwa

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15. **በሥራ ላይ ሳይውል የቀረ የእርዳታ ገንዘብ እና ንብረት**

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ለእርዳታና መልሶ ማቋቋም ስራ ታስቦ ተሰብስቦ በስራ ላይ ሳይውል የቀረ ገንዘብና ንብረት በዚህ አዋጅ ወደ ፈንዱ ተዛውሯል።

16. **የለጋሾች መብት**

ለፈንዱ ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት በገንዘብም ሆነ በዓይነት የሰጡት ሐብት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የመጠየቅ መብት ይኖራቸዋል።

17. **ስለሒሳብ መዛግብት**

1. ፈንዱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የፈንዱ የሒሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም ዋና ኦዲተር በሚወክላቸው ሌሎች ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራል። የኦዲተሮች የምርመራ ውጤት በየዓመቱ መጨረሻ ለምክር ቤቱ ይቀርባል።

18. **ተፈፃሚነት የሌላው ሕግና አሰራር**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ ለተሸፈነ ጉዳይ ተፈጻሚነት የለውም።

19. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

1. የመስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል።
2. ምክር ቤቱ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት

cinaancho 1 garinni fultanno wodho loosu aana hosiisate biddissa fushshara dandaanno.

የወጣ ደንብን ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

20. **Lallawu Loosu Aana Hosanno Yanna**

Kuni lallawi Woxawaajje 20, 2014 M.D hanafe loosu aana hosanno.

20. **አዋጁ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፳ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

**Hawaasa, Woxawaajje 20, 2014 M.D**

**ሀዋሳ፣ ነሐሴ ፳ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር**